# በስጦታችን ማገልገል

በመጋቢ እስጢፋኖስ አለሙ
ጁን 04, 2026

**ማውጫ**

1. ስጦታ

**የውይይት ጥያቄዎች፡-**

- መንፈሳዊ ስጦታ ምን ማለት ነው?
- መጽሐፍ ቅዱስ መንፈሳዊ ስጦታን እንዴት ይገልጻል?
- መንፈሳዊ ስጦታ ተብሎ የሚጠራው ምንድን ነው?
- መንፈሳዊ ስጦታዎች ከተፈጥሮ ችሎታዎች የሚለዩት በምንድን ነው?
  -

2. የስጦታ ምንጭ

**የውይይት ጥያቄ፡-** መንፈሳዊ ስጦታዎችን ለአማኞች የሚያድለው ማን ነው?

3. ስጦታችንን መለየት

**የውይይት ጥያቄ፡-** እግዚአብሔር የሰጠንን ስጦታ ለማወቅ ምን ማድረግ አለብን?

4. ስጦታና ዓላማው

**የውይይት ጥያቄዎች፡-** እግዚአብሔር በጸጋው የሰጠንን መንፈሳዊ ስጦታ ለይተን አውቀን ተገንዝበናል ወይ?
የመንፈሳዊ ስጦታዎች ዓላማ ምንድን ነው?
ስጦታችንን ለምን እንጠቀምበታለን?

5. ስለ ስጦታችን በዙርያችን ያሉ የበሰሉ መንፈሳዊ ሰዎች ምን ይላሉ

**የውይይት ጥያቄ፡-** እግዚአብሔር በሕይወታችን ላይ ያስቀመጣቸው መንፈሳዊ መሪዎች ስለ ስጦታችንና ስለ አገልግሎት ጥሪያችን ምን ያያሉ? ምን ይናገራሉ?

6. ስጦታና ማበረታታት

**የውይይት ጥያቄ፡-** ስጦታችሁን እንድታውቁና እንድትጠቀሙበት ያበረታቷችሁን ሰዎች አስታውሱ። እኛስ በዙሪያችን ያሉ ሰዎች ስጦታቸውን እንዲያውቁና እንዲያዳብሩ ምን እያደረግን ነው?

7. ስጦታና ትጋት

**የውይይት ጥያቄ፡-** እግዚአብሔር በአደራ የሰጠንን ስጦታና ዕድል በትጋትና በታማኝነት ስራ ላይ እያዋልነው ነው?

8. ስጦታና ስልጠና

**የውይይት ጥያቄ፡-** ክርስቶስ ደቀ መዛሙርቱን ለመሪነት ለማዘጋጀት ምን ዓይነት መንገድ ተጠቀመ?

9. ስጦታና ባህሪ

**የውይይት ጥያቄ፡-** እግዚአብሔር በሕይወታችን ያኖረውን ስጦታ ለማሳደግ ምን ዓይነት ሥልጠና ያስፈልገናል?
ያንን ስጦታ ለቤተ ክርስቲያን ጥቅም እንዴት እየተጠቀማችሁበት ነው?
ስጦታዎቻችሁን በትሕትና እና በፍቅር ለመጠቀም ምን ማድረግ ያስፈልጋል?

10. ሥጦታና ሥርዓት

**የውይይት ጥያቄዎች፦**

- መንፈሳዊ ስጦታዎችን መለማመድ ለምን በሥርዓት መሆን አለበት?
- መንፈሳዊ ስጦታዎች ያለ ሥርዓት ሲለማመዱ ምን ችግሮች ሊፈጠሩ ይችላሉ?
- 1ኛ ቆሮንቶስ 14፡40 "ሁሉ በአግባቡና በሥርዓት ይሁን" የሚለው በቤተክርስቲያን አገልግሎት ውስጥ ምን ትርጉም አለው?
- ሥርዓት መንፈስን ያጠፋል ወይስ ጤናማ የሆነ የስጦታ አጠቃቀምን ይረዳል?
- መሪዎች ስለ ነፍሳችን እንደሚተጉ ማወቃችን ለእነርሱ ያለንን አመለካከት እንዴት ሊቀይረው ይገባል?

11. በስጦታችን በፍቅር ማገልገል

**የውይይት ጥያቄዎች፦**

- አገልግሎታችን በእውነተኛ ፍቅር የተመሰረተ ነው? ወይስ ፍቅር የጎደለው ከንቱ ድካም ሆኖ ቀርቷል?
- እኔ የማገለግለው ከክርስቶስ ፍቅር ተነስቼ ነው ወይስ ከሌላ ተነሳሽነት?

12. ስጦታና ሌሎችን የመተካት ባህል

**የውይይት ጥያቄዎች፦**

- የእኛ አገልግሎት ዘመን ሲያልቅ አገልግሎቱ እንዲቀጥል ምን እያደረግን ነው?
- የመተካት ባህል በአገልግሎታችን ውስጥ እየገነባን ነው?
- ከእኛ በኋላ አገልግሎቱ እንዲቀጥል ሰዎችን/ቀጣይ ትውልድን እያዘጋጀን፣ እያፈራ፣ እያበቃን፣ እያሰለጠንን እና እያሰማራን ነው?

እስካሁን በአገልጋዮች ስብሰባ ላይ የሰጠሁት ስልጠናዎች ማጠቃለያ ነጥቦችና የውይይት ጥያቄዎች በተከታታይ በጹሑፍ አቀርባለው። በተሰጡት ትምህርቶች ላይ በመመስረት ባላችሁበት የአገልግሎት ክፍል ውስጥ እነዚህን ጥያቄዎች ራስን ለመመልከትና/ለመገምገም ደግሞም ባላችሁበት የአገልግሎት ክፍል ጋር ካሉት ጋር እንድትወያዩበት የተዘጋጀ ነው። ስለዚህ የሁሉ ራስ የሆነው ክርስቶስ በሰጠን ስጦታዎች  በኩል በሚሰጠን ምሪትና እንክብካቤ  አካሉ "እየተያያዘና እየተጋጠመ፣ እያንዳንዱ ክፍል የራሱን ሥራ እያከናወነ በፍቅር ያድጋል፤ ራሱንም ያንጻል" (ኤፌ.4፡16)

እያንዳንዱ የአገልግሎት ክፍል እና በየቤቱ ያሉት የቤት ለቤት አገልግሎት ክፍሎች - ግባችንን የምናሳካበት ዕቅዳችንን የምንፈጽምበት መንገድ (ስትራቴጂ) ናቸው። እንዴት ደቀመዝሙር እናድርግ? የሚለውንም ጥያቄ ይመልሳሉ። የአገልግሎት ዘርፎችና የቤት ለቤት አገልግሎት ዓላማ ደቀመዝሙር ለማፍራት ነው።

"ስለዚህ ከእግዚአብሔር **ምሕረት የተነሣ ይህ አገልግሎት ስላለን** ተስፋ አንቈርጥም።" 2 ቆሮ. 4፥1
"13 እኛ ግን ከመጠን በላይ አንመካም፤ የምንመካው **እግዚአብሔር በመደበልንና** እስከ እናንተም እንኳ በሚደርሰው **የአገልግሎታችን ወሰን ነው**። 14 የክርስቶስን ወንጌል ይዘን ወደ እናንተ በመጣን ጊዜ፣ ከተመደበልን የአገልግሎት ወሰን አላለፍንም።  15 ደግሞም ሌሎች በደከሙበት ሥራ ከመጠን በላይ በመመካት ከተመደበልን ወሰን አናልፍም፤ ይልቁንም እምነታችሁ እያደገ በሄደ ቍጥር በእናንተ ዘንድ **የተመደበልን አገልግሎት እየሰፋ እንደሚሄድ ተስፋ እናደርጋለን**" 2 ቆሮ 10፡13-15

ይሄ ቪዲዮ ላይ ስላነሳዋቸው 5ቱ የአገልግሎት አእማዶች ቀጣዩን ጽሁፍ እልካለው። ይህንን በጸሎት ሆናችሁ እንድታነቡት በትህትና እጠይቃለው።

# በስጦታችን ማገልገል

1. **ስጦታ**

- ስጦታ ከእግዚአብሔር ለአማኞች እንዲያው በጸጋው ለአገልግሎትና ቤተ ክርስቲያኝ ለማነጽና ለመገንባት የሚሰጥ በረከት ነው።
- እግዚአብሔር በቤተክርስቲያን ውስጥ እያንዳንዱ የአካል ክፍል ላይ ሊጋራ ጥቅም ጸጋን ሰጥቷል። 1 ቆሮ. 12፡7
- ስጦታ የአንድን አማኝ መንፈሳዊነት መለኪያ አይደለም።
- አያስመኩም "**ብቃታችን ከእግዚአብሔር ነው** እንጂ፥ በገዛ እጃችን እንደሚሆን አንዳችን እንኳ ልናስብ ራሳችን የበቃን አይደለንም" 2 ቆሮ. 3፡5 "**አንተ እንድትበልጥ ማን አድርጎሃል? ያልተቀበልኸውስ ምን አለህ? የተቀበልህ ከሆንህ ግን እንዳልተቀበልህ የምትመካ ስለ ምንድር ነው?**" 1 ቆሮ. 4፡7 ሊሆኑ አይችሉም
- ስጦታችን ሌላውን በፍቅር የምናገለግልበት እንጂ ከሌላው የምንበልጥበት አይደለም።
- ስጦታችንን ዋጋ ከፍለን አልገዛናቸውም። ዋጋ የምንከፍለው ለጠቀበልነው ወይንም ላገኘነው ነገር ነው።
- ስጦታችን መወዳደርያ/መፎካከርያ አይደሉም።
- አንድ ሰው በተፈጥሮ ጥሩ ተናጋሪ ወይም አስተዳዳሪ ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን መንፈሳዊ ስጦታ በመንፈስ ቅዱስ የሚሰጥ ልዩ ኃይልና ችሎታ ነው። የአማኝ ስጦታ ጸጋን ይሸከማል።
- እያንዳንዱ ዳግመኛ የተወለደ አማኝ ቢያንስ አንድ መንፈሳዊ ስጦታ እንዳለው እና ያ ስጦታ የክርስቶስ አካል ለማነጽና ለአገልግሎት እንደተሰጠው ሊገነዘብ ያስፈልገዋል።
- ሁሉም ስጦታዎች በመጨረሻ ሥልጣን ባለው በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረት ይፈተናሉ።
- መንፈሳዊ ልምምዳችን ከመጽሐፍ ቅዱስ በላይ አይደለም።
- በአገልግሎት ውስጥ በጣም ብዙ ኃላፊነት እየወሰዱ ያሉ ሰዎች እነርሱ ራሳቸው አገልግሎቱን ሊመሩ ይገባል።

**የውይይት ጥያቄዎች፡-**

- መንፈሳዊ ስጦታ ምን ማለት ነው?
- መጽሐፍ ቅዱስ መንፈሳዊ ስጦታን እንዴት ይገልጻል?
- መንፈሳዊ ስጦታ ተብሎ የሚጠራው ምንድን ነው?
- መንፈሳዊ ስጦታዎች ከተፈጥሮ ችሎታዎች የሚለዩት በምንድን ነው?

2. **የስጦታ ምንጭ**

- "6 ከሁሉ በላይ የሚሆን **በሁሉም የሚሠራ በሁሉም የሚኖር አንድ አምላክ የሁሉም አባት** አለ። 7 ነገር ግን **እንደ ክርስቶስ ስጦታ መጠን ለእያንዳንዳችን ጸጋ ተሰጠን።** 8 ስለዚህ። ወደ ላይ በወጣ ጊዜ ምርኮን ማረከ ለሰዎችም **ስጦታን ሰጠ** ይላል። 9 ወደ ምድር ታችኛ ክፍል ደግሞ ወረደ ማለት ካልሆነ፥ ይህ ወጣ ማለትስ ምን ማለት ነው? 10 ይህ የወረደው ሁሉን ይሞላ ዘንድ ከሰማያት ሁሉ በላይ የወጣው ደግሞ ያው ነው። 11 እርሱም አንዳንዶቹ ሐዋርያት፥ ሌሎቹም ነቢያት፥ ሌሎቹም ወንጌልን ሰባኪዎች፥ ሌሎቹም እረኞችና አስተማሪዎች እንዲሆኑ **ሰጠ**፤ 12 -13 ሁላችን የእግዚአብሔርን ልጅ በማመንና በማወቅ ወደሚገኝ አንድነት፥ ሙሉ ሰውም ወደ መሆን፥ የክርስቶስም ሙላቱ ወደሚሆን ወደ ሙላቱ ልክ እስክንደርስ ድረስ፥ **ቅዱሳን አገልግሎትን ለመሥራትና ለክርስቶስ አካል ሕንጻ ፍጹማን ይሆኑ ዘንድ።**" ኤፌ. 4፡6-13
- "**በጌታ የተቀበልኸውን አገልግሎት** ከፍጻሜ ለማድረስ ተጠንቀቅ" ቆላ. 4፡17
- እውነተኛ ደስታና ውጤታማ አገልግሎት የሚመጣው ስጦታውን የሰጠንን ጌታንና የተሰጠን ስጦታ አውቀን ስናገለግልበት ነው።
- እግዚአብሔር ስጦታን ይሰጣል። አገልግሎትን ይሰጣል። በሮችን ይከፍታል። ሞገስንና መከናወንን ይሰጣል።

**የውይይት ጥያቄ፡-** መንፈሳዊ ስጦታዎችን ለአማኞች የሚያድለው ማን ነው?

3. **ስጦታን መለየት**

ስጦታን ለመለየት ምን ማደረግ አለብን?

- መጸለይ
- በተለያዩ አገልግሎቶች ክፍል ገብቶ መሞከር
- ከሌሎች አማኞች ምስክርነት/ማረጋገጫ ማግኘት
- ስለ ስጦታ ማጥናት
- ስጦታን  መጠቀም
- የሚያፈራውን ፍሬ ማየት/መመዘን

- "እንግዲህ፥ ወንድሞች ሆይ፥ **ሰውነታችሁን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝና ሕያው ቅዱስም መሥዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ** በእግዚአብሔር ርኅራኄ እለምናችኋለሁ፥ እርሱም **ለአእምሮ የሚመች አገልግሎታችሁ** ነው።

  [2] የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም በጎና ደስ የሚያሰኝ ፍጹምም የሆነው ነገር ምን እንደ ሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ። [3] **እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ የእምነትን መጠን እንዳካፈለው፥ እንደ ባለ አእምሮ እንዲያስብ እንጂ ማሰብ ከሚገባው አልፎ በትዕቢት እንዳያስብ በመካከላችሁ ላለው ለእያንዳንዱ በተሰጠኝ ጸጋ እናገራለሁ።** [4] በአንድ አካል ብዙ ብልቶች እንዳሉን፥ የብልቶቹም ሁሉ ሥራ አንድ እንዳይደለ፥ [5] እንዲሁ ብዙዎች ስንሆን በክርስቶስ አንድ አካል ነን፥ እርስ በርሳችንም እያንዳንዳችን የሌላው ብልቶች ነን። [6] **እንደ ተሰጠንም ጸጋ ልዩ ልዩ ስጦታ አለን፤** ትንቢት ቢሆን እንደ እምነታችን መጠን ትንቢት እንናገር፤ [7] አገልግሎት ቢሆን በአገልግሎታችን እንትጋ፤ የሚያስተምርም ቢሆን በማስተማሩ ይትጋ፤ [8] የሚመክርም ቢሆን በመምከሩ ይትጋ፤ የሚሰጥ በልግስና ይስጥ፤ የሚገዛ በትጋት ይግዛ፤ የሚምር በደስታ ይማር።" ሮሜ 12፥1-7

**የውይይት ጥያቄ፦ እግዚአብሔር የሰጠንን ስጦታ ለማወቅ ምን ማድረግ አለብን?**

## 4. ስጦታና ዓላማው

መንፈሳዊ ስጦታዎች የተሰጡት፦

- ቤተክርስቲያን ማነጽ (1ኛ ቆሮ. 14፥12)
- ሌሎችን ለማገልገል (1ኛ ጴጥ. 4፥10)
- ለክርስቶስ አካል እድገት (ኤፌ. 4፥11-13)
- ለእግዚአብሔር ክብር ነው (1ኛ ጴጥ. 4፥11)
- "10 ልዩ ልዩን የእግዚአብሔርን ጸጋ ደጋግ መጋቢዎች እንደ መሆናችሁ፥ **እያንዳንዳችሁ የጸጋን ስጦታ እንደ ተቀበላችሁ መጠን በዚያው ጸጋ እርስ በርሳችሁ አገልግሉ፤** 11 ማንም ሰው የሚናገር ቢሆን፥ እንደ እግዚአብሔር ቃል ይናገር፤ የሚያገለግልም ቢሆን፥ እግዚአብሔር በሚሰጠኝ ኃይል ነው ብሎ ያገልግል፤ ክብርና ሥልጣን እስከ ዘላለም ድረስ ለእርሱ በሚሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል **እግዚአብሔር በነገር ሁሉ ይከብር ዘንድ፤** አሜን።" 1 ጴጥ. 4፥10-11

**የውይይት ጥያቄ፦ እግዚአብሔር በጸጋው የሰጠንን መንፈሳዊ ስጦታ ለይተን አውቀን ተገንዝበናል ወይ?**
የመንፈሳዊ ስጦታዎች ዓላማ ምንድን ነው?
ስጦታችንን ለምን እንጠቀምበታለን?

## 5. ስለ ስጦታችን በዙርያችን ያሉ የበሰሉ መንፈሳዊ ሰዎች ምን ይላሉ?

- ለመሪዎች ራስንና አገልግሎትና ማሳየት አስፈላጊ ነው።
- የአገልግሎት ምስክርነት "2 እንደ ተገለጠልኝም ወጣሁ፤ **ምናልባትም በከንቱ እንዳልሮጥ ወይም በከንቱ ሮጬ እንዳልሆን** በአሕዛብ መካከል የምሰብከውን ወንጌል **አስታወቅኋቸው፤** ዋኖች ግን መስለው ለሚታዩ ለብቻቸው

አስታወቅኋቸ ው። … 7 ተመልሰው ግን ጴጥሮስ ለተገረዙት የሆነው ወንጌል አደራ እንደ ተሰጠው እንዲሁ ለእኔ ላልተገረዙት የሆነው ወንጌል አደራ **እንደ ተሰጠኝ አዩ፤** 8 ለተገረዙት ሐዋርያ እንዲሆን ለጴጥሮስ የሠራለት፥ ለእኔ ደግሞ ለአሕዛብ ሐዋርያ እንድሆን ሠርቶአልና። 9 ደግሞ የተሰጠኝን ጸጋ አውቀው፥ አዕማድ መስለው የሚታዩ ያዕቆብና ኬፋ ዮሐንስም እኛ ወደ አሕዛብ እነርሱም ወደ ተገረዙት ይሄዱ ዘንድ ለእኔና ለበርናባስ **ቀኝ እጃቸውን ሰጡን፤** 10 ድሆችን እናስብ ዘንድ ብቻ ለመኑን፥ ይህንም ደግሞ ላደርግ ተጋሁ።" ገላ. 2፡2 ፤ 2፡7-10

- የሕይወት ምስክርነት ፡- የኢየሩሳሌም ቤተክርስቲያን ሐዋርያትና ሽማግሌዎች ምስክርነት ስለ በርናባስና ጳውሎስ "ስለ ጌታችን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ስም **ነፍሳቸውን ከሰጡት ከምንወዳቸው ከበርናባስና ከጳውሎስ** ጋር የተመረጡትን ሰዎች ወደ እናንተ እንልክ ዘንድ በአንድ ልብ ሆነን ፈቀድን።" *ሐሥ* 15፡26
- የቅዱሳን ምስክርነት ስለ ጢሞቴዎስ "ለእርሱም በልስጥራንና በኢቆንዮን ያሉ **ወንድሞች መሰከሩለት።**" ሐ. ሥ. 16፡2

- "ኢየሩሳሌም በደረሱ ጊዜም፣ ቤተ ክርስቲያንና ሐዋርያት እንዲሁም ሽማግሌዎች ተቀበሏቸው፤ የተላኩትም ***እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር ሆኖ የሠራውን ሁሉ ነገሯቸው።***"*ሐሥ* 15፡5 አ.መ.ት.
- *"[26] ከዚያም ስለ ፈጸሙት ሥራ ለእግዚአብሔር ጸጋ አደራ ወደ ተሰጡበት ወደ አንጾኪያ በመርከብ ሄዱ። [27] በደረሱም ጊዜ ቤተ ክርስቲያኑን ሰብስበው* ***እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር ያደረገውን ሁሉ ለአሕዛብም የሃይማኖትን ደጅ እንደ ከፈተላቸው ተናገሩ።*** *[28] ከደቀ መዛሙርትም ጋር አያሌ ቀን ተቀመጡ።" ሐሥ* 14፡26-28

- ስለ ሕይወታችንም ፣ ስለ አገልግሎታችንም እንዲሁም ስለ ስጦታችን የበሰሉ አማኞች ምስክርነት እጅግ አስፈላጊ ነው።

**የውይይት ጥያቄ፡-** እግዚአብሔር በሕይወታችን ላይ ያስቀመጣቸው መንፈሳዊ መሪዎች ስለ ስጦታችንና ስለ አገልግሎት ጥሪያችን ምን ያያሉ? ምን ይናገራሉ?

## 6. ስጦታና ማበረታታት

- በዙርያችን ያሉ ሰዎች እግዚአብሔር በሰጣቸው ስጦታ ይበልጥ ይጠቅሙ ዘንድ ምን ያህል እያበረታታናቸው ነው?
- **በርናባስ ጳውሎስን** "22 ሳውል ግን እየበረታ ሄደ፥ በደማስቆም ለተቀመጡት አይሁድ ይህ ክርስቶስ እንደ ሆነ አስረድቶ መልስ ያሳጣቸው ነበር። 23 ብዙ ቀንም ሲሞላ አይሁድ ሊገድሉት ተማከሩ፤ 24 ሳውል ግን አሳባቸውን አወቀ። ይገድሉትም ዘንድ በሌሊትና በቀን የከተማይቱን በር ሁሉ ይጠቀብቁ ነበር፤ 25 ደቀ መዛሙርት ግን በሌሊት ወስደው በቅጥር ላይ አሳልፈው በቅርጫት አወረዱት። 26 ***ሳውልም ወደ ኢየሩሳሌም በደረሰ ጊዜ ከደቀ መዛሙርት ጋር ይተባበር ዘንድ ሞከረ፤*** ሁሉም ደቀ መዝሙር እንደ ሆነ ስላላመኑ ፈሩት። 27 **በርናባስ ግን ወስዶ ወደ ሐዋርያት አገባውና** ጌታን በመንገድ እንዴት እንዳየውና እንደ ተናገረው በደማስቆም **በኢየሱስ ስም ደፍሮ እንዴት እንደ ነገረ ተረከላቸው።** 28 በጌታም በኢየሱስ ስም ደፍሮ እየተናገረ በኢየሩሳሌም ሲወጣና ሲገባ ከእነርሱ ጋር ነበረ።" *ሐሥ*. 9፡26-28
- **ጳውሎስ ጢሞቴዎስን** "4 **እንባህን** እያሰብሁ በደስታ እሞላ ዘንድ ላይህ እናፍቃለሁ። 5 በአንተ ያለውን ግብዝነት የሌለበትን **እምነትህን** አስባለሁ፤ ይህም እምነት ቀድሞ በአያትህ በሎይድ በእናትህም በኤውንቄ ነበረባቸው፥ በአንተም ደግሞ እንዳለ ተረድቼአለሁ። 6 ስለዚህ ምክንያት፥ እሳት እንደሚያቀጣጥል ሰው፥ እጆቼን በመጫኔ **በአንተ ያለውን የእግዚአብሔርን ስጦታ** እንድታነሣሣ አሳስብሃለሁ። 7 እግዚአብሔር የኃይልና የፍቅር ራስንም የመግዛት መንፈስ እንጂ የፍርሃት መንፈስ አልሰጠንምና።" 2 ጢሞ. 1፡4-7
- **ጵርስቅላና አቂላ አጵሎስን "**26 እርሱም በምኵራብ ገልጦ ይናገር ጀመር። ጵርስቅላና አቂላም በሰሙት ጊዜ፥ ወስደው የእግዚአብሔርን መንገድ ከፊት ይልቅ በትክክል ገለጡለት። 27 እርሱም ወደ አካይያ ማለፍ በፈቀደ ጊዜ፥ ***ወንድሞቹ አጸናኑት፥ ይቀበሉትም ዘንድ ወደ ደቀ መዛሙርት ጻፉለት፤*** በደረሰም ጊዜ አምነው የነበሩትን በጸጋ እጅግ ይጠቅማቸው ነበር፤ 28 ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ እንደ ሆነ ከመጻሕፍት እየገለጠ ለአይሁድ በሁሉ ፊት በጽኑ ያስረዳቸው ነበርና።" *ሐሥ* 18፡26-28
- **ሙሴ ኢያሱን** "7 ፤ ሙሴም ኢያሱን ጠርቶ በእስራኤል ሁሉ ፊት። አንተ ከዚህ ሕዝብ ጋር እግዚአብሔር ለአባቶቻቸው እንዲሰጥ ወደ ማለላቸው ምድር ትገባለህና፥ እርስዋንም ለእነርሱ ታወርሳለህና **ጽና፥ አይዞህ። 8 ፤ በፊትህም የሚሄድ እርሱ እግዚአብሔር ነው፤ ከአንተ ጋር ይሆናል፥ አይጥልህም፥ አይተውህም፤ አትፍራ፥ አትደንግጥ አለው።**" ዘዳግም 31፡7-8

**የውይይት ጥያቄ፡-** ስጦታችሁን እንድታውቁና እንድትጠቀሙበት ያበረታቷችሁን ሰዎች አስታውሱ። እኛስ በዙሪያችን ያሉ ሰዎች ስጦታቸውን እንዲያውቁና እንዲያዳብሩ ምን እያደረግን ነው?

## 7. ስጦታና ትጋት

- እግዚአብሔር የሰጠንን መንፈሳዊ ጸጋ (መክሊት) በትጋት ልናገለግልበት ይገባል።
- ስጦታችን ቸል አለማለት
- **በስጦታችን እንደግ** - የእግዚአብሔርን የእኛ ድርሻ ልዩነት እንወቅ።
- "ኢያሱም የእስራኤልን ልጆች አላቸው። የአባቶቻችሁ አምላክ **እግዚአብሔር የሰጣችሁን ምድር ትወርሱ ዘንድ እስከ መቼ ለመግባት ቸል ትላላችሁ?"** ኢያሱ 18፡3
- "ልጆቼ ሆይ፥ **በእግዚአብሔር ፊት ትቆሙና ታገለግሉት ዘንድ፥ አገልጋዮቹም ትሆኑና ታጥኑለት ዘንድ እግዚአብሔር መርጦአችኋልና ቸል አትበሉ።"** 2 ዜና 29፡11
- "6 ስለዚህ ምክንያት፥ እሳት እንደሚያቀጣጥል ሰው፥ እጆቼን በመጫኔ **በአንተ ያለውን የእግዚአብሔርን ስጦታ እንድታነሣሣ አሳስብሃለሁ።** 7 እግዚአብሔር የኃይልና የፍቅር ራስንም የመግዛት መንፈስ እንጂ የፍርሃት መንፈስ አልሰጠንምና።" 2 ጢሞቴዎስ 1፡6-7

- **የቸልታ ትርጉም፡-**
    - **ቸል ማለት** - አይቶ እንዳላዩ መሆን - ፊትን ማዞር ዓይንን መከደን - ራስን መደበቅ - ራስን ማራቅ - ተገቢ ነገርን ከማድረግ ማፈግፈግ - ወደ ኋላ ማለት - ገሸሽ ማለት - መሸሽ - መተው - መስነፍ - መቦዘን - ጀምሮ መተው - ማቋረጥ - አለመጨረስ - ከአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ መዝገብ ቃላት የተወሰደ።
- **ቸልታ** - ስንፍና ፣ ማታለል ፣ ልግሚያ ፤ በግድ የለሽነት የሚደረግ ነገር ነው። ኤር 48፡10 "የእግዚአብሔርን ሥራ በቸልታ የሚያደግ ርጉም ይሁን"
- **ታካች** - ለመሥራት ፈቃደኛ ያልሆነ ፍላጎቱም ያልተሟላለት ሰነፍ ሰው ነው። (10፡26፤ 13፡4፤ 15፡29፤ 19፡24 ፤22፡13 ፤ 24፡30 ፤ 26፡13-16)

## ታካች ወይም ሰነፍ ሰው - ከመጽሐፈ ምሳሌ

- "30 በታካች ሰው እርሻ፥ አእምሮ በጐደለውም ሰው ወይን ቦታ አለፍሁ። 31 እነሆም፥ ሁሉ እሾህ ሞልቶበታል፥ ፊቱንም ሳማ ሸፍኖታል፥ የድንጋዩም ቅጥር ፈርሶአል። 32 ተመለከትሁና አሰብሁ፤ አየሁትና ተግሣጽን ተቀበልሁ።" ምሳ 24፡30-32
- ሥራውን በወቅቱ የማይጀምር (6፡9-10 ፤ 22፡13)
    - በወቅትህ/በዘመንህ ምን እያደረግክበት ነው
- "ታካች ሰው **በብርድ ምክንያት** አያርስም፤ ስለዚህ በመከር ይለምናል፥ ምንም አያገኝም።" ምሳ 20፡4
- ታካች የጀመረውን የማይፈጽም (12፡27)
- ታካች ከባድ ሥራ የሚያመልጥበትን መንገድ የሚፈልግ ነው (2፡4)
- ሰነፍ መሬቱን የማያርስ - በተሰጠው ላይ የሚተኛ ነው - ምሳ 12፡11 ፤ 12፡24)
    - ትጋት ሁከት ፣ ጩኸት ወይንም ሚዛንን ያልጠበቀ ሩጫ አይደለም።
- የድኽነት መፍትሔው ታታሪነት ነው (ምሳ. 10፡4 ፤ 12፡11 ፤ 14፡23 ፤ 28፡19)
- ሰነፍ **አጥብቆ ይመኛል** አንዳች አያገኝም የትጉዎች ምኞት ግን ይረካል - ምሳ 13፡4) ትጋት ትርፍን ያስገኛል
- "ታካች ሰው። **አንበሳ በሜዳ ነው፤ በመንገዱ ላይ እሞታለሁ ይላል።**" ምሳ 22፡13
- " የትጉ ሰው እቅድ ወደ ትርፍ ያመራል" 21፡5
- "ታካችን የሚገድለው ምኞቱ ነው **እጆቹ መሥራት አይፈልጉምን**" ምሳ 21፡25
- በወቅትህ - በመሬትህ - በዕድልህ በአግባቡ ተጠቀም!

**የውይይት ጥያቄ፡- እግዚአብሔር በአደራ የሰጠንን ስጦታና ዕድል በትጋትና በታማኝነት ስራ ላይ እያዋልነው ነው?**

### 8. ስጦታና ስልጠና

- ስጦታ የእግዚአብሔር ስጦታ ነው፤ ስልጠና የሰው ምላሽና ኃላፊነት ነው።
- ስጦታ ቢኖርም ያለ ስልጠና ሙሉ ፍሬ ላያፈራ ይችላል፤ ስልጠናም ቢኖር ያለ ስጦታ የአገልግሎትን ጥሪ ሊተካ አይችልም። ጤናማ አገልጋይ ሁለቱንም ያስፈልገዋል።
- የመጀመሪያው ቤተክርስቲያን መሪዎች በድንገት የተፈጠሩ አልነበሩም። ክርስቶስ ራሱ በረጅም ጊዜ ያዘጋጃቸውና ያሰለጠናቸው መሪዎች ነበሩ።
    - ከመጥምቁ ዮሐንስ አገልግሎት የተዘጋጁ

- ○ አንዳንዶቹ ደቀ መዛሙርት ከክርስቶስ ጋር ከመሄዳቸው በፊት በመጥምቁ ዮሐንስ አገልግሎት ተዘጋጅተው ነበር።
- ○ “ስለዚህ ከዮሐንስ ጥምቀት ጀምሮ... ከእነዚህ አንዱ ከእኛ ጋር የትንሣኤው ምስክር ይሆን ዘንድ ይገባል።” (ሐዋርያት 1፡22)

ደቀ መዛሙርቱ:-

- ከክርስቶስ ጋር የኖሩ
- አገልግሎቱን የተመለከቱ
- ትምህርቱን የሰሙ
- በተግባር የተለማመዱ
- አንድ በአንድ በግል የተመከሩና የታረሙ ነበሩ

ከትንሣኤው በኋላ የ40 ቀን ስልጠና

- ስለ መንግሥቱ አስተማራቸው
  - ○ “ደግሞ አርባ ቀን እየታያቸው ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ነገር እየነገራቸው...” (ሐዋርያት 1፡3)

**መጻሕፍትን** እንዲያስተውሉ አእምሯቸውን ከፈተ!

- “በዚያን ጊዜም መጻሕፍትን ያስተውሉ ዘንድ አእምሮአቸውን ከፈተላቸው።” (ሉቃስ 24፡45)

በአንድነት **በጸሎት** ተጉ

- “እነዚህ ሁሉ... በአንድ ልብ ሆነው ለጸሎት ይተጉ ነበር።” (ሐዋርያት 1፡14)
- ከመላካቸው በፊት:-
- በጸሎት ተጉ
- በአንድነት ቆዩ
- የእግዚአብሔርን ጊዜ ጠበቁ

በኢየሩሳሌም ጠበቁ

- “በሁሉም **መንፈስ ቅዱስ** ሞላባቸው።” (ሐዋርያት 2፡4)
- ከመሪነታቸው በፊት የመንፈስ ቅዱስ ኃይልን ታጠቁ።

**የውይይት ጥያቄ፡-** ክርስቶስ ደቀ መዛሙርቱን ለመሪነት ለማዘጋጀት ምን ዓይነት መንገድ ተጠቀመ?

**9. ስጦታና ባህሪ**

- እግዚአብሔር ስጦታን ይሰጣል፤ ባህሪን ግን በደቀ መዛሙርትነት፣ በፈተና፣ በመታዘዝና በጊዜ ይገነባል።
- ባህሪ ወሳኝ ነው። ባህሪያችን ሲቀረጽ የክርስቶስን መልክ ማንጸባረቅ ይጀምራል። አገልግሎታችን ብዙ ርቀት መሄድ ይችላል።
- ክርስቶስ ደቀ መዛሙርቱን:
  - ○ በትሕትና
  - ○ በፍቅር
  - ○ በታማኝነት
  - ○ በመታዘዝ ምሳሌ በመሆን አስተምሯቸዋል።

ደቀመዛሙርቱን ከመላኩ በፊት ባህሪያቸውን ቀርጿል።

- “27 ሁሉ ከአባቴ ዘንድ ተሰጥቶኛል፤ ከአብ በቀር ወልድን የሚያውቅ የለም፥ ከወልድም በቀር ወልድም ሊገለጥለት ከሚፈቅድ በቀር አብን የሚያውቅ የለም። 28 እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ፥ ወደ እኔ ኑ፥ እኔም አሳርፋችኋለሁ። 29 ቀንበሬን በላያችሁ ተሸከሙ **ከእኔም ተማሩ፥ እኔ የዋህ በልቤም ትሑት ነኝና፥ ለነፍሳችሁም ዕረፍት ታገኛላችሁ፤** 30 ቀንበሬ ልዝብ ሸክሜም ቀሊል ነውና።” ማቴዎስ 11፡27-30
-

መንፈሳዊ ሕይወቴ እያደገ ነው ወይ? በባህሪዬና በአገልግሎቴ ላይ ጌታን መምሰል ይንጸባረቃል ወይ?

- "መንፈሳዊ ስጦታዎችን ፈልጉ፣ ነገር ግን ከሁሉ በላይ ፍቅርን ተከተሉ። 1 ቆሮ. 12፡31 ፤ 14፡1
- “በእናንተ ዘንድ ሁሉ በፍቅር ይሁን።” 1 ቆሮ 16፡14
  - ○ ያለፍቀር የሆነ አገልግሎት

- አገልግሎት ተቀባዩን አያንጽም
- አገልጋዩ ከእግዚአብሔር የሚቀበለው ብድራት የለውም
- እግዚአብሔርን አያከብርም

ባለሁበት የአገልግሎት ክፍል ውስጥ ስጦታዬን አውቄ ሌሎችን እያበረታታው እድል እየሰጠው ሆን ብዬ ራሴን ለመተካት ምን አይነት ጥረት እያደረግኩ ነው?

**የውይይት ጥያቄ፦** እግዚአብሔር በሕይወታችን ያኖረውን ስጦታ ለማሳደግ ምን ዓይነት ሥልጠና ያስፈልገናል?
ያንን ስጦታ ለቤተ ክርስቲያን ጥቅም እንዴት እየተጠቀማችሁበት ነው?
ስጦታዎቻችሁን በትሕትና እና በፍቅር ለመጠቀም ምን ማድረግ ያስፈልጋል?

### 10. *ሥጦታና ሥርዓት*

*መንፈሳዊ ስጦታዎችን መለማመድ ለምን በሥርዓት መሆን አለበት?*

- 1ኛ ቆሮንቶስ 14፡40 "ሁሉ በአግባቡና **በሥርዓት** ይሁን" የሚለውን እንዴት ትረዳላችሁ?
- "17ለመሪዎቻችሁ ታዘዙ፤ ተገዙላቸውም። ምክንያቱም እነርሱ **በብርቱ የሚያስጠይቃቸው ነገር ስላለባቸው፣ ስለ ነፍሳችሁ ጕዳይ ይተጋሉ**። ስለዚህ ሥራቸውን በሐዘን ሳይሆን በደስታ ማከናወን እንዲችሉ ታዘዟቸው። አለበለዚያ አይበጃችሁም" ዕብ. 13፡17

**የውይይት ጥያቄ፦**

- *መንፈሳዊ ስጦታዎችን መለማመድ ለምን በሥርዓት መሆን አለበት?*
- *መንፈሳዊ ስጦታዎች ያለ ሥርዓት ሲለማመዱ ምን ችግሮች ሊፈጠሩ ይችላሉ?*
- 1ኛ ቆሮንቶስ 14፡40 "ሁሉ በአግባቡና በሥርዓት ይሁን" የሚለው በቤተክርስቲያን አገልግሎት ምን ትርጉም አለው?
- *ሥርዓት መንፈስን ያጠፋል ወይስ ጤናማ የሆነ የስጦታ አጠቃቀምን ይረዳል?*

## 11. በስጦታችን በፍቅር ማገልገል

- "በእናንተ ዘንድ ሁሉ በፍቅር ይሁን።" 1 ቆሮ 16፡14
- ፍቅር ጥሎ ማገልገል - የማያንጽ - ሽልማት የሌለው - ከንቱ ድካም ነው። ፍቅር በሌለበት ፍሬ የለም።
  - ያለፍቅር የሆነ አገልግሎት ባዶ የሆነ አገልግሎት ነው።
    - አገልጋዩ ድካሙ/ልፋቱ/ድርጊቱና እንቅስቃሴው ሁሉ ዋጋ ቢስ ይሆናል - ያለ ብድራት - ከንቱ የማይጠቅም ነው።
    - አገልግሎት ተቀባይ አይታነጽም ጭራሽ  በማጉረምረም ይሞላል።
    - እግዚአብሔር በአገልግሎቱ አልከበረም።
- ፍቅር ውስጣችን ጨለማ እንዳይወርሰን እግዚአብሔር ለውስጣችን የሰጠን የሕይወት ብርሃን ነው።
- "21 እኔ ጳውሎስ ይህን ሰላምታ በገዛ እጄ ጽፌአለሁ። 22 ጌታን ኢየሱስ ክርስቶስን የማይወድ ቢኖር የተረገመ ይሁን። ጌታችን ሆይ፥ ና። 23 የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከእናንተ ጋር ይሁን። 24 ፍቅሬ በክርስቶስ ኢየሱስ ከሁላችሁ ጋር ነው። አሜን።" 1 ቆሮ 16፡21-24
- 
- ነገር ግን እውነትን በፍቅር እየያዝን በነገር ሁሉ ወደ እርሱ ራስ ወደሚሆን ወደ ክርስቶስ እንደግ፤" ኤፌ 4፡15
- "33 **እኔ ደግሞ ብዙዎቹ ይድኑ ዘንድ ለጥቅማቸው እንጂ የራሴን ጥቅም ሳልፈልግ በሁሉ ነገር** ሰውን ሁሉ ደስ እንደማሰኝ፥ ለአይሁድም ለግሪክም ሰዎች ለእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንም ማሰናከያ አትሁኑ።" 1 ቆሮ 10፡33
- ፍቅር የግል ነጻነትን በፈቃደኝነት መገደብን ያስተምረናል።
- ፍቅር በሁኔታዎች ውስጥ የምናሳየው ባህሪ ነው።
- ፍቅር መኖሪያችን - መታወቅያችን ነው  - ዮሐ 13፡35
- 1ኛ ቆሮንቶስ 13 እንደሚያስተምረው ፍቅር ከስጦታዎች ለምን ይበልጣል?

ብዙ ስጦታ ያለው ሰው ፍቅር ከሌለው ምን ይጎድለዋል?

"በሰዎችና በመላእክት ልሳን ብናገር **ፍቅር ግን ከሌለኝ እንደሚጮኽ ናስ ወይም እንደሚንሽዋሽዋ ጸናጽል ሆኜአለሁ።**
2 ትንቢትም ቢኖረኝ ምሥጢርንም ሁሉና እውቀትን ሁሉ ባውቅ፥ ተራሮችንም እስካፈልስ ድረስ እምነት ሁሉ ቢኖረኝ **ፍቅር ግን ከሌለኝ ከንቱ ነኝ**። 3 ድሆችንም ልመግብ ያለኝን ሁሉ ባካፍል፥ ሥጋዬንም ለእሳት መቃጠል አሳልፌ ብሰጥ **ፍቅር ግን ከሌለኝ ምንም አይጠቅመኝም።** 4 ፍቅር ይታገሣል፥ ቸርነትንም ያደርጋል፤ ፍቅር አይቀናም፤ ፍቅር አይመካም፥ አይታበይም፤ 5 የማይገባውን አያደርግም፥ የራሱንም አይፈልግም፥ አይበሳጭም፥ በደልን አይቆጥርም፤ 6 ከእውነት ጋር ደስ ይለዋል እንጂ ስለ ዓመፃ ደስ አይለውም፤ 7 ሁሉን ይታገሣል፥ ሁሉን ያምናል፥ ሁሉን ተስፋ ያደርጋል፥ በሁሉ ይጸናል። 8 ፍቅር ለዘወትር አይወድቅም፤ ትንቢት ቢሆን ግን ይሻራል፤ ልሳኖች ቢሆኑ ይቀራሉ፤ እውቀትም ቢሆን ይሻራል።" 1 ቆሮ. 13፡1-8

| + | - |
|---|---|
| 1. ፍቅር ይታገሣል (እየተጎዱ አለመበቀል)<br>2. ቸርነትንም ያደርጋል (ለጉዳት ምላሽ ደግነት)<br>3. ከእውነት ጋር ደስ ይለዋል (በእውነትም ላይ አትዋሹ ያቆ 3፡14)<br>4. ሁሉን ይታገሣል (የግል ነጻነትን በፈቃደኝነት መገደብ) "ሁሉንም ነገር ይታገሳል"<br>5. ሁሉን ያምናል (በቀላሉ መታለልን ሳይሆን ሰፊ በሆነ ልብ ሌሎችን መቀበልን ያመለክታል) ተጠራጥሪ አይደለም<br>6. ሁሉን ተስፋ ያደርጋል (ለበዳዩ ሁለተኛ እድልን ይሰጣል)<br>7. በሁሉ ይጸናል (ተስፋዎች በተደጋጋሚ አሳዛኝ በሚሆኑበት ጊዜ በድፍረት ይጠባበቃል)<br>8. ፍቅር ለዘወትር አይወድቅም (ምንም አይጎድልህም) | 1. ፍቅር **አይ**ቀናም (በተሰጠው አትቅና)<br>2. ፍቅር **አይ**መካም (ስለተሰጠህ አትመካ) ታይታ የሞላበት ጉራ የሚል ደባል ትሩጉም አለው። እውቀት ያስታብያል<br>3. **አይ**ታበይም ("የተነፋ") ከ 4፡6,18,19፤ 5፡2፤ 8፡1 ይለያል<br>4. የማይገባውን **አያ**ደርግም (ተገቢ ያልሆነ ተግባር)<br>5. የራሱንም **አይ**ፈልግም፥ (ሁኔታን ያገናዘብ የግል ጥቅም ፍለጋ የሚደረግ እንቅስቃሴ)<br>6. **አይ**በሳጭም (ስስ የሆነ ስሜት የለውም ፣ ከሥር የተደበቅ ወይም ለጥቃት ያኮበኮብ አይደለም)<br>7. በደልን **አይ**ቆጥርም (በደል ሲፈጸምበት፡ ከፋት ባለበት)<br>8. ስለ ዓመፃ ደስ **አይ**ለውም (የሀሰት መቆርቆር) |

*"[7] ወዳጆች ሆይ፥ ፍቅር ከእግዚአብሔር ስለ ሆነ፥ የሚወደውም ሁሉ ከእግዚአብሔር ስለ ተወለደ እግዚአብሔርንም ስለሚያውቅ፥ እርስ በርሳችን እንዋደድ። [8] **ፍቅር የሌለው እግዚአብሔርን አያውቅም፥ እግዚአብሔር ፍቅር ነውና።***
*[9] በዚህ የእግዚአብሔር ፍቅር በእኛ ዘንድ ተገለጠ፥ በእርሱ በኩል በሕይወት እንኖር ዘንድ እግዚአብሔር አንድ ልጁን ወደ ዓለም ልኮታልና። [10] ፍቅርም እንደዚህ ነው፤ እግዚአብሔር እርሱ ራሱ እንደ ወደደን ስለ ኃጢአታችንም ማስተስሪያ ይሆን ዘንድ ልጁን እንደ ላከ እንጂ እኛ እግዚአብሔርን እንደ ወደድነው አይደለም። [11] ወዳጆች ሆይ፥ እግዚአብሔር እንዲህ አድርጎ ከወደደን እኛ ደግሞ እርስ በርሳችን ልንዋደድ ይገባናል። [12] እግዚአብሔርን ማንም ከቶ አላየውም፤ እርስ በርሳችን ብንዋደድ እግዚአብሔር በእኛ ይኖራል ፍቅሩም በእኛ ፍጹም ሆኖአል። [13] ከመንፈሱ ስለ ሰጠን፥ በእርሱ እንድንኖር እርሱም በእኛ እንዲኖር በዚህ እናውቃለን። [14] እኛም አይተናል አባትም ልጁን የዓለም መድኃኒት ሊሆን እንደ ላከው እንመሰክራለን።*
*[15] ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ በሚታመን ሁሉ እግዚአብሔር በእርሱ ይኖራል እርሱም በእግዚአብሔር ይኖራል።*
*[16] እኛም እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ፍቅር አውቀናል አምነንማል። እግዚአብሔር ፍቅር ነው፥ በፍቅርም የሚኖር በእግዚአብሔር ይኖራል እግዚአብሔርም በእርሱ ይኖራል። [17] በፍርድ ቀን ድፍረት ይሆንልን ዘንድ ፍቅር በዚህ ከእኛ ጋር ተፈጽሞአል፤ እርሱ እንዳለ እኛ ደግሞ እንዲሁ በዚህ ዓለም ነንና። [18] ፍጹም ፍቅር ፍርሃትን አውጥቶ ይጥላል እንጂ በፍቅር ፍርሃት የለም፥ ፍርሃት ቅጣት አለውና፤ የሚፈራም ሰው ፍቅሩ ፍጹም አይደለም። [19] እርሱ አስቀድሞ ወዶናልና እኛ እንወደዋለን። [20] ማንም። እግዚአብሔርን እወዳለሁ እያለ ወንድሙን ቢጠላ ሐሰተኛ ነው፤ ያየውን ወንድሙን የማይወድ ያላየውን እግዚአብሔርን ሊወደው እንዴት ይችላል? [21] እግዚአብሔርንም የሚወድ ወንድሙን ደግሞ እንዲወድ ይህች ትእዛዝ ከእርሱ አለችን።"* 1 ዮሐ 4:7-21

***የውይይት ጥያቄዎች፡-***

- **አገልግሎታችን በእውነተኛ ፍቅር የተመሰረተ ነው? ወይስ ፍቅር የጎደለው ከንቱ ድካም ሆኖ ቀርቷል?**
- **እኔ የማገለግለው ከክርስቶስ ፍቅር ተነስቼ ነው ወይስ ከሌላ ተነሳሽነት?**

## 12. ስጦታና ሌሎችን የመተካት ባህል

- አገልግሎታችን በእኛ ላይ ብቻ እንዳይመሰረት ወይንም እኛ ስናቆም አብሮ የሚቆም ሥራ እንዳይሆን ራሳችንን መተካታ አለብን። ብዙ መሪዎች ራሳቸውን የማይተኩ ከሆነ አገልግሎታቸው በእነርሱ ላይ ብቻ ይመሰረታል። መጽሐፍ ቅዱስ ግን ጤናማ አመራር ማለት ሌሎችን ማብቃት፣ ኃላፊነትን ማካፈል እና የሚተኩ መሪዎችን ማፍራት እንደሆነ ያስተምራል።
    - የሙሴና የዮቶር ታሪክ (ዘፀአት 18) ስለ ውጤታማ የመተካት ባህል አስፈላጊ መርሆችን ያሳያል።

የዮቶር ምክር - "ይህ የምታደርገው መልካም አይደለም፤ አንተም ከአንተ ጋር ያለውም ሕዝብ ፈጽሞ ትደክማላችሁ።" (ዘፀ. 18፡17-18)

ችግሩ
- ሁሉን ጉዳይ ሙሴ ራሱ ይፈታ ነበር
- ሕዝቡ ረዥም ሰልፍ ይጠብቅ ነበር
- ሙሴም ይደክም ነበር

መፍትሄው

- "ከሕዝቡም ሁሉ ችሎታ ያላቸውን ሰዎችን ምረጥ..." (ዘፀ. 18፡21)
- ለሎችን መለየት፣ ማሳየት፣ ማሰልጠን፣ ዕድል መስጠት፣ ማገዝ፣ መታገስ፣ ማብቃት
- ሌሎች በአገልግሎት ላይ ስህተትን እየሰሩ እንዲማሩ እድል መስጠት

ኃላፊንትን ማካፈል - ዮቶር ሙሴን፡-

- የሺህ አለቆች
- የመቶ አለቆች
- የሃምሳ አለቆች
- የአሥር አለቆች እንዲሾም መከረው።

### ውጤቱ

- ሥራው ተከፋፈለ
- ሕዝቡ በፍጥነት ተገለገለ
- መሪዎች ተባዙ
- ሙሴም ሸክም ቀለለት - አለጊዜው ሩጫው አልተቃጠለም

መርሆቹ
- በትክክለኛ ጊዜ ለትክክለኛ ሰዎች ኃላፊነትን መስጠት
- ሙሴ - ሰዎችን ለይቶ አወቀ፣ አመነ፣ ኃላፊነት ሰጣቸውና እንዲያድጉ እድል ሰጣቸው
- ሙሴ ሁሉን ነገር መቆጣጠር ቢፈልግ ኖሮ ይህን ምክር ሊቀበል አይችልም ነበር።
- የመተካት ባህል ዘላቂ አገልግሎትን ይፈጥራል።

የመተካት ባህል ማለት ከእኛ በኋላ የሚቀጥል አገልግሎት ለመገንባት ሰዎችን ማብቃትና ማሰማራት ነው።

**የውይይት ጥያቄዎች፡-**

- **የእኛ አገልግሎት ዘመን ሲያልቅ አገልግሎቱ እንዲቀጥል ምን እያደረግን ነው?**
- **የመተካት ባህል በአገልግሎታችን ውስጥ እየገነባን ነው?**
- **ከእኛ በኋላ አገልግሎቱ እንዲቀጥል ሰዎችን/ቀጣይ ትውልድን እያዘጋጀን፣ እያፈራ፣ እያበቃን፣ እያሰለጠንን እና እያሰማራን ነው?**

-

“ስለዚህ የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ፤ ጸንታችሁ ቁሙ፤ በምንም ነገር አትናወጡ። ለጌታ ሥራ ዘወትር የምትተጉ ሁኑ፤ ምክንያቱም ለጌታ የምትደክሙት በከንቱ እንዳልሆነ ታውቃላችሁ” 1 ቆሮ. 15:58

“ባለ ዐደራዎችም ታማኝ ሆነው መገኘት አለባቸው።” 1 ቆር 4፡2



# የመንፈሳዊ ስጦታዎች የአዲስ ኪዳን ዝርዝር

| 1 ቆሮ 12፡8-11 | 1 ቆሮ 12፡28 | ሮሜ 12፡6-8 | ኤፌ 4፡11 | 1 ጴጥ 4፡11 |
|---|---|---|---|---|
| 1. የጥበብ ቃል | 1. ሐዋርያት | 1. ትንቢት | 1. ሐዋርያት | 1. ንግግር |
| 2. የእውቀት ቃል | 2. ነቢያት | 2. አገልግሎት | 2. ነቢያት | 2. አገልግሎት |
| 3. እምነት | 3. አስተማሪዎች | 3. ማስተማር | 3. ወንጌላውያን | |
| 4. የፈውስ ስጦታዎች | 4. ታምራት አድራጊዎች | 4. ምክር | 4. እረኞች | |
| 5. ታምራት ማድረግ | 5. የመርዳት ስጦታ | 5. ልግሥና | 5. አስተማሪዎች | |
| 6. ትንቢት መናገር | 6. አስተዳደር | 6. መሪነት | | |
| 7. መናፍስትን መለየት | 7. ልሳናት | 7. ምሕረት ማድረግ | | |
| 8. የልሳናት ዓይነቶች | | | | |
| 9. ልሳናትን መተርጎም | | | | |

በሁሉም ሰዎች ሁሉን የሚሰራ እግዚአብሔር አንድ ነው።